# አርቲስት ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ ተወዳጅ ነበር



አርቲስት ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ በ61 ዓመቱ ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ የቀብሩም ሥነ-ሥርዓት በማግስቱ ቅዳሜ ሐምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ከቀኑ በ10 ሰዓት በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ወዳጅ ዘመዶቹና በርካታ አድናቂዎቹ በተገኙበት ተፈጽሟል፡፡

በጥር ወር 12ኛ ቀን 1940 ዓ.ም. በሐረርጌ ክ/ሀገር ወበራ አውራጃ፣ በጐሮ ጉቱ ወረዳ፣ ልዩ ስሙ መካኒሳ በተባለው ሥፍራ የተወለደው አርቲስቱ፤ ባለትዳር እና የአንድ ሴት ልጅ አባት ነበረ፡፡

ሻለቃ ወጋየሁ በቀድሞ የኢትዮጵያ ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ አብዛኛውን የዕድሜ ዘመኑን አገልግሏል፡፡ በኤርትራ፣ በሐረርና በአዲስ አበባ በሚገኙ የሠራዊቱ ታዋቂ የሙዚቃ የቴአትር ክፍል ውስጥ ከፍተኛ ሚና እና የኃላፊነት ቦታ የነበረው አርቲስቱ፤ በዜማና ግጥም ደራሲነቱ፣ በድምፃዊነቱ፣ በቴአትር አዘጋጅነቱና ተዋናይነቱ፣ በቴክኒሻንነቱና በአዛዥነቱ የሚታወቅ አንጋፋ ባለሙያ ነበረ፡፡ ባለቤቱ ወ/ሮ ምሥራቅ ኃይሉ ወጋየሁ ደግነቱ በኩላሊት ህመም ታሞ ይሰቃይ በነበረበት ጊዜ ቅን የሆነ ወገናዊ ትብብራቸውን ላደረጉለት በሀገር ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በሙሉ ላቅ ያለ ምስጋና አቅርበዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት ወጋየሁ ደግነቱ በሕንድ ከፍተኛ የኩላሊት ማዛወር ሕክምና ከተደረገለት በኋላ በመልካም ጤንነት ለ5 ዓመታት ያህል ቆይቷል፡፡ ከሁለት ወር በፊት ባጋጠመው ድንገተኛ የጤና ችግር ምክንያት በሕክምና ሲረዳ የቆየ መሆኑን ያሳወቁት ወ/ሮ ምሥራቅ፣ የሀዘናቸው ተካፋይ የሆኑትን ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይከፈላችሁ ብለዋል፡፡

## የአርቲት ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ፤ አጭር የሕይወት ታሪክ

### ከጥር 1940 እስከ ሐምሌ 2001 ዓ.ም.

አርቲስት ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ፤ ከአባቱ ከአቶ ደግነቱ ጅማ ከእናቱ ከወ/ሮአበራሽ ወዳጆ ጥር 12 ቀን 1940 ዓ.ም. በሐረርጌ ክ/ሀገር በወበራ አውራጃ በጐሮ ጉቱ ወረዳ ልዩ ስሙ መካኒሳ በተባለው ስፍራ ተወለደ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በሐረር ልዑል መኮንን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትሏል፡፡ በነበረው ልዩ የሙዚቃ ፍቅር የተነሳ መጋቢት 1 ቀን 1955 ዓ.ም. በሐረርጌ ክ/ሀገር ፖሊስ ሙዚቃ ክፍል በታዳጊነት ዕድሜው ተቀጠረ፡፡ ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅና ተፈቃሪ ድምፃዊ ለመሆን የበቃው ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ፤ በ1959 ዓ.ም. ከድምፃዊነቱ በተጨማሪ የሐረር ፖሊስ ሙዚቃ ክፍል የተወዛዋዥ ቡድን አሰልጣኝ፣ የዜማና የግጥም ደራሲ ሆኗል፡፡

ይኸው ለኪነ-ጥበብ ያለው ፍቅር እየጐለበተ፣ እያበበና እየጐመራ በመሄዱ ወጋየሁ… በቀድሞ ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በ1960ዎቹ የተውኔት ባለሞያና አዘጋጅ፣ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች ቴክኒሻን ጭምር በመሆን

የዘርፈ ብዙ ባለሞያዎች ባለቤት መሆኑን ለባልደረቦቹ እና ለአለቃዎቹ ማሳየት ችሏል፡፡ ከሙዚቃ ስራው በተጓዳኝ የአቋረጠውን ትምህርት በማታው የትምህርት ክፍል በመከታተል ለተጨማሪ እውቀት የነበረውን ትጋትም አሳይቷል፡፡ በ1964 ዓ.ም. የሙሉ 10 አለቅነት ማዕረግ ያገኘው ወጋየሁ፤ ቀጥሎም የመኮንንነትን ኮርስ በሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ በመውሰድ ሚያዚያ 14 ቀን 1968 ዓ.ም. በምክትል መቶ አለቃነት ማዕረግ ተመርቋል፡፡ በፖሊስ ሠራዊት ባልደረባነቱ ወቅት በቀድሞ ኤርትራ ክ/ሀገርና በመላው ሀገሪቱ ተዘዋውሮ በሙያው ሀገሩን ያገለገለው ወጋየሁ፤ ኤርትራ ውስጥ በነበረው በ5ኛ ሻለቃ ፈጥኖ ደራሽ ሠራዊት ውስጥ የመቶ መሪ በመሆን ወቅቱ የጠየቀውን ሀገራዊ ግዳጅ ተወጥቷል፡፡ ሀገሩና ወገኖቹ ሁሉ ሊዘነጉት የማይቻላቸውን የጀግንነት ተግባርም በወጣት መኮንንነቱ የተዋጊ አዋጊነት ዘመን ፈጽሟል፡፡

ስለ እናት ኢትዮጵያ ክብር "የደስታሽ ሕይወት ተካፋይ፣ ለችግርሽ ሆኜ ተወካይ፣ መቆሜን አውቃለሁ ጠንቅቄ፣ ታሪክሽን ለማኖር ጠብቄ…" ብሎ ያዜመው፣ ስለ ወላጅ እናት ፍፁምነት እና መተኪያ አልባነት "የሰው የእንስሣት የአራዊት… እናት እኮነች መድኃኒት" በማለት ያንጐራጐረው እና "አርኬ የሁማ…" በተሰኘው ማሕበረሰባዊ ተወዳጅ የኦሮሚኛ ዜማው የሚታወቀው ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ፤ ከጦር ግንባር ግዳጅ መልስ በመስከረም ወር 1969 ዓ.ም. የኤርትራ ክ/ሀገር ፖሊስ ሙዚቃ ክፍል አዛዥ ሆኖ አገልግሏል፡፡ በ1978 ዓ.ም. የሻለቅነት ማዕረግ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ እና ከዚያም በኋላ በኪነ-ጥበብና በፖሊሳዊ ሙያው ከሐረርጌ ጫፍ እስከ አሰብና የቀድሞይቱ ኢትዮጵያ ደሴቶች ድረስ በመነቃነቅ ከእሱ ይጠበቅ የነበረውን የዜግነት ድርሻ ተወጥቷል፡፡ አርቲስት ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ፤ በቀድሞ የኢትዮጵያ ፋናንስ ፖሊስ፣ የፖሊስ ሠራዊት የሙዚቃና የቴአትር እንደዚሁም በአዲስ አበባ ፖሊስ መምሪያ የ6ኛ ፖሊስ ጣቢያ የወንጀል መከላከል ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሰርቷል፡

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ፋኩልቲ በማታው የትምህርት ክፍል የህግ ሙያን በመከታተል በ1984 ዓ.ም. ወርሐ ታህሣስ የህግ ዲፕሎማውን የተቀበለው አርቲስት ወጋየሁ ደግነቱ ጅማ፤ በጥብቅናና በህግ አማካሪነት ሙያ ሕብረተሰቡን በቅንነት ሲያገለግል የቆየ ስሙ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነበረ፡፡ በሳቂታነቱ፣ የተጣሉትን በማስታረቅ ተግባሩ፣ በተግባቢነቱና በጨዋታ አዋቂነቱ፣ በሥራ እና በወገን ወዳድነቱ በኢትዮጵያዊን ዘንድ ልዩ አክብሮትን ያገኘ ሰው ነበረ፡፡ ሻለቃ ወጋየሁ ባለትዳር እና የአንድ ሴት ልጅ አባት እንደዚሁም የአንድ ወንድ ልጅ አያት ሲሆን፤ ከወራት በፊት በአጋጠመው የጤና መታወክ ምክንያት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በ61 ዓመቱ አርብ ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ የቀብር ስነ-ሥርዓቱም ቅዳሜ ሐምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ወዳጅ ዘመዶቹና በርካታ አድናቂዎቹ በተገኙበት ከቀኑ በ10 ሰዓት ተፈጽሟል፡፡

- ቤተሰቦቹ፡- ታሞ ህክምና እየተከታተለ በነበረበት ሰዓትም ሆነ በሐዘናቸው ጊዜ ከጐናቸው ላልተለዩ የአርቲስቱ ልባዊ ወዳጆች እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የከበረ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡

To contact family, call 0111 11 87 01

Cellphone 0911 47 92 58 - 0911 47 15 71 - 0911 41 46 73 - 0913 20 83 09